# ለዶ/ር ብርሃኑ ነጋና መሰሎቹ
# የኢትዮጵያ ታሪክ ሀ ሁ እነሆ !

አቶሰውየው ባላገሩ (ከሰሜን አሜሪካ)

ከአንድ ወር ተኩል በፊት በሰሜን አሜሪካ አርሊንግተን ከተማ ቨርጂኒያ ሸራተን ሆቴል ውስጥ፣ የግንቦት ሰባት መሪ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና በእንግድነት ተናጋሪ ሆኖ የቀረበው ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው የኦነግን መሪ ዶ/ር ኑር ደዴፎን አጅበው ካቀረቡልን ንግግሮች መካከልና ካሳዘኑኝ መልዕክቶች አንዱ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የማይጨውን ጦርነት ለኢትዮጵያውያን ውርደትና ሽንፈት አድርጎ ማቅረቡ ነበር ። አዎን በዚያ ንግግሩ መንደርደሪያ ስለኢትዮጵያ ታሪክ የተላያዩ ሰዎች የተለያዩ ትርጉሞችን ሊሰጡት እንደሚችሉ ***"የኢትዮጵያ ታሪክ ኮንቴስትድ ነው"*** በማለት ከመንደርደሪያው አስቀምጦ ነበርና ስለማይጨው የሰጠው አስተያየት እንግዲህ የሱ ትርጓሜ አለያም የወቅቱ ፖለቲካ ሸሪኮቹን ኦነግና ኦብነግን ለማስደሰት ብሎ ከጥቂት ወራት በፊት አብሮ መሥራት በሚል ዘይቤ በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚያደርገው ዘመቻ አንዱ ተቀጢላ ክፍል ነው ማለት ነው። ለማንኛውም ሁልጊዜም ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ የተለያዩ ትርጉሞችና አመለካከቶች ሲነሱ ጥያቄው መሆን ያለበት ተርጓሚው ማነው? ዓላማውስ ብለን መጠየቃችን የማይቀር ነው። እንግዲህ ዶ/ሩ በዚህ ንግግሩ ስለኢትዮጵያዊነትና ስለዜግነት የተውገረገረ ባዶ የፍልስፍና ንግግሩ ምናልባትም ዛሬ ዛሬ ልክ ከዘሬ ሃያ ዓመት በፊት ሰልፉን ከጸረ - ኢትዮጵያ ኃይላት ከወያኔና ከሻቢያ እንዳደረገ ሁሉ ዛሬ ደግሞ ሰልፉን ከነ ኦነግና ኦብነግ ጋር አድርጓልና ስለማይጨው ትክክል ያልሆነ ትርጉምና አቀራረብ ይዞልን ብቅ ሲል ብዙዎች ወገኖችን ያጠያየቀ ጉዳይ እንደሆነ እንዲረዳልኝ እወዳለሁ። በተለይም ደግሞ እንደ ዶ/ሩ ዓይነት ሲናገር ሁሉንም ዕውነት ነው ብለው የሚያደምጡ ወጣት ወገኖቻችንን የሚያነሆልል ስለሆነ በዚህ ጽሑፌ ዕውነተኛውን ታሪክ በማቅረብ የማይጨው ታሪክ አያቶቻችን ለኢትዮጵያዊነት ከባድ መስዋዕትነት የከፈሉበት ልንኮራበትና ልንበረታታበት የሚገባ ታሪካችን አንጂ ዶ/ሩ በንግግሩ እንዳቀረበው የምንናፍርበት እንዳልሆነ የሚያስረዳውን እውነተኛ ታሪክ ከነማስረጃው እነሆ፦

አባቶቻችን የዛሬዩቱን ኢትዮጵያን ያስረከቡን አልጋ ባልጋ ሄደው ተሚልቶላቸው ወይም ደግሞ ዶ/ር ብርሃኑ በዚሁ ንግግሩ ውስጥ ስለ ኢትዮጵያዊነትና ስለ ዜግነት ሲንበዛበዝበት በነበረው መላ ቅጡ በጠፋ ፍልስፍና ሊያስረዳን እንደሞከረው፣ **"ጭቆና በበዛበት ሀገር ኢትዮጵያዊነት ሊኖር አይችልም"** በማለት እንዳውገረገረው ሳይሆን ጠላት ሲመጣ የባላባቱ ሥርዓት በድሎኛልና አንዘምትም ያሉበት ጊዜ በታሪክ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም። ታሪክ የሚነግረን ግን ኢትዮጵያውያን ወራሪ ኃይል መጣ በሚባልበትና ክተት ሲባል አባቶቻችን ለአቅመ አዳም የደረሱ ሁሉ ተጠራርተው ሆ ! ብለው ወደ ጦር ሜዳ በመሄድ ግዳጃቸውን ይወጡ እንደ ነበርና ሁልጊዜም አቸናፊ ሆነው የሚመጡበት ባይሆንም የምንኮራበት የመስዋዕትነት ታሪካችን ነው። እንግዲህ የማይጨው ታሪክ ለምን ኢትዮጵያውያን የማናፍርበት ታሪክ እንደሆነ የሚያስረዳውን በሚቀጥለው ላቅርብ።

በመጀመሪያ ኢትዮጵያ የ 1896 ቱ የአድዋ ጦርነት አቸናፊ መሆን በመላው አፍሪካ ካሉት ሀገሮች በሙሉ የአውሮፓውያንን የአፍሪካን ክፍል አህጉር መቀራመት ዘመቻ በመግታት እንደ ሀገር የቀጠለች ብቸኛዋ ሀገር ብትሆንም፣ ጣልያን በእንግሊዞች እርዳታ የኢትዮጵያን ወደብ ከተቆጣጠረችበት ከምጽዋ ጀምሮ ቀስ በቀስ ወደ ውስጥ በመስፋፋት ኤርትራ ብላ የጠራቻትን የሰሜን

ኢትዮጵያን ግዛት ባሕረ ነጋሽን ማስለቀቅ ያልተቻለበት ሁናቴ ነበር። በነገራችን ላይ ኢትዮጵያውያን ያንንም መስፋፋት ዝም ብለው አልተቀበሉም ነበር። ወደ ኋላ ታሪክን ብንመለከት የዛሬዎቹ የኤርትራ ገዢዎች የማይቀበሉትና ከታሪክ መጽሐፍ ሊሰርዙት የሚይችሉት ለምሳሌ የራስ አሉላ 1885 በዶጋሌ ላይ በጣልያን ላይ የተጎናጸፋት ድል ኢትዮጵያውያን የከፈሉት የመስዋዕትነትና ሌላው የምንኮራበት በትግል የተጎናጸፋት ታሪካችን ነው። ራስ አሉላ ይህንን ድል ከመጎናጸፋቸው በፊት ከጣልያን ጋር ከምጽዋ ሠላሣ ኪ/ሜ ርቀት ላይ በመጀመሪያው ዙር ጦራቸው ቢመታና ቢያፈገፍጉም የዶጋሌው ድል ተመልሰው የተጎናጸፋት እንደሆነ ለመጥቀስ እፈልጋለሁ ። በአጠቃላይ አባቶቻችን አቅማቸው እስከ ፈቀደ ድረስ በጊዜው የመጣ ኃይል ምንም የማይበገር ቢሆንም ፤ በትጥቅም ከነሱ በሚሊዮን ጊዜ ቢበልጥም የሚጠበቅባቸውን ኢትዮጵያዊ ግዳጅ ይወጡት ነበር እንጂ ዛሬ ዛሬ እነ ዶ/ር ተብዬዎቹ ሊያስተምሩን እንደሚቃጡት ሊቋቋሙት የማይቻላቸው ኢትዮጵያዊነትን ገዳይ ጠላት ሲመጣባቸው የምናሸንፈው ጠላት ስላልሆን አቅፈን እናሸሞንሙነው ያሉበት ጊዜ አልነበረም።

በ 1922 ዓ.ም. ሞሶሎኒ ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ በፊት በ 1906 ዓ.ም. በጊዜው የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይና የጣልያን መንግሥታት የኢትዮጵያን ጉዳይ በሚመለከት ጣልያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመጠቅለል ፍላጎቷ እንደተጠበቀ መሆኑን ቢተማመኑም፤ እንግሊዝ እስከ 1925 ዓ.ም. ድረስ ይህንን የጣልያንን ፍላጎት የምትቀበለው የምዕራብ ኢትዮጵያን በመውሰድ ከአጎራባች ሀገሮች የቅኝ ግዛቶቿ ጋር በመጠቅለል በጣና ሐይቅ ላይ ግድብ የምትሠራበት ሁናቴ እስከ ተፈጠረ ጊዜ ድረስ እንደነበርና፤ ፈረንሳይ ደግሞ በጅቡቲ የቅኝ ግዛቷ የኤኮኖሚ ጥቅም ልታገኝበት የምትችለው የኤኮኖሚ ትስስሯን ከመሃል ኢትዮጵያ ጋር በማጠናከር ነው ብቻ መሆኑን ጠንቅቃ ታውቅ ስለነበር ኢትዮጵያ በጣልያን እንድትዋጥ አትደግፈውም ነበር። ይህ ሁናቴ እንግዲህ ለኢትዮጵያ አመቺ ሁናቴን ፈጥሮ እንደነበረ መገመት አያዳግትም። ይህን ጽሁፍ በማዘጋጀት ላይ እያለሁ ከዚህ በላይ ያቀረብኩትን የኢትዮጵያውያን ጸረ-የቅኝ አገዛዝ ትንቅንቅ ዕውነተኛ ታሪክ አሌ የሚል እነብርሃኑ ነጋ ኢትዮጵያዊነቱን የሚመሠክሩለት ኦነግ ለተባበሩት መንግሥታት ካቀረበው ደብዳቤ ውስጥ እንደሚከተለው አንብበው የራስዎን ግንዛቤ እንዲወስዱ እየጋበዝኩ ወደ ታሪኩ እመለሳለሁ

*Mr. Secretary General*

*We would like to reiterate that the OLF is a legitimate organization leading the Oromo people's national struggle against the colonial regime of Ethiopia. Its goal is to enable the Oromo people to exercise their fundamental right to self-determination, the right upheld by the international community and the UN. Furthermore, it works to lay a new foundation for peaceful and harmonious relations among the peoples of the Horn in general and in Ethiopia in particular, where peoples could live together in peace and engage in their own social and human resource development.*

*The OLF vehemently oppose all forms of terrorism and reject terrorism as a form of struggle for the genuine and noble cause of the liberation of a people under occupation. We denounce Ethiopian state terrorism and other forms of terrorism since they destroy individuals, families, communities, institutions, and societies by violating human rights.*

*Mr. Secretary General:*

*For more than a century and half, the Oromos have lived under the brutal colonial rule of the Abyssinian/Ethiopian, that together with European colonizers, created the Ethiopian state during the European colonial era of Africa. (*09-08-2011*)*

http://www.oromoliberationfront.org/News/2011/OLF_Letter_to_UN_General_Secretary.pdf

*ከዚህ በላይ ያለው የእንግሊዝኛ ጽሁፍ የተገኘው የኦነግ ድሕረ-ገጽ ላይ ነው። በተለይ ጽሁፉ ኢትዮጵያ በኤውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች የተቋቋመች ናት የሚለውን ከላይ ያቀረብኩትን ታሪክ በጭንቅላቱ የሚያቆመውን የታሪክ ብረዛ ለማሳየትና ቀደም ብዬ እንዳሳሰብኩት ዶ/ር*

*ብርሃኑ "**የኢትዮጵያ ታሪክ ኮንቴስትድ ነው**" ብሎ ሊያስተምረን የሞከረው አባባል ይሄን የመሰለውን ሳንጠይቅ እንድንቀበል ሊያመቻቹን ጥረታቸው የት ድረስ እንደሚሄድ ለወገኖቼ ለማሳወቅ ነው*

ሞሶሎኒ ኢትዮጵያን በማንኛውም አይነት መንገድ የመጠቅለል ህልሙ እያደገ ከአጼ ኃይለ ሥላሤ ጋር በሮማ ከተማ በ 1924 ዓ.ም. ከተገናኝና በ 1928 ዓ.ም. የጋራ ስምምነት በሚል ሽፋን ወደ ውስጥ በኤኮኖሚ ተራድኦ እግሩን ሊያስገባ ቀዳዳ በመሻት ተራድኦን በማቁለጭለጭ ለምሳሌ ከአሰብ – ደሴ መንገድ የመሥራት ሃሳብ በማቅረብ የመዋዋ ዝግጅቱን ሲያሟሙቅ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በጊዜው የነበረውን የዓለም ሁናቴና የጣልያንን ፍላጎት በደንብ የተረዱ ነበርና፤ የጣልያን ወደድኳችሁ ዘፈን አልተዋጠላቸውም ነበር። ስለሆነም የጣልያን መንግሥት በጦርነት ያልቻለውን በኤኮኖሚ መንገድ ማለሳለስና በእጁ የማስገባት ወጥመድ ውስጥ ሊገቡለት አልቻሉም፤ ቀዝቀዝ አሉበት። ይህም የማዘናጋት ጥረት የማይሠራ መሆኑን የተረዳው ሞሶሎኒ ኢትዮጵያን በኃይል ለመያዝ በቁርጥ ወሰነ። በተለይ በ 1930 ቱ የዓለም ኃያላን አሠላለፍ በተቀዳሚ የአንደኛው ዓለም ጦርነትን በመተባበር አቸናፊ የነበሩት እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና አሜሪካ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተሸናፊ የነበረችው ጀርመን በወቅቱ የናዚ አስተዳደር ጡንቻዋ እያዳር እያደገ ስለነበር የናዚ ጀርመንን እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት ወቅት ሲሆን በተለይ እንግሊዝና ፈረንሳይ እንደ 1906 ቱ ጊዜ ጣልያን ኢትዮጵያን በመዋዋ በኩል ታሳይ ስለነበረው ፍላጎት እንደበፊት ግድ የለንም ሳይሆን ጣልያንን ለማስደሰት ወደኋላ የማይሉ ለመሆናቸው አያጠራጥርም ነበር። በእርግጥ ኢትዮጵያ ከ 1923 ዓ.ም. ጀምሮ የሊግ ኦፍ ኔሽን አባል የነበረች ብትሆንም የኋላ ኋላ ግን ያንንም ደፍጥጠው ፈረንጆቹ ኢትዮጵያ በጣልያን እጅ እንድትወድቅ ሁናቴን ያመቻቹበትን ታሪካዊ ወቅት ቀጠል አድርጌ አቀርባለሁ። ይህንን ሁናቴ የፈጠረው ደግሞ የጣልያን ፋሺሽት ፍልስፍና የናዚ ጀርመኒን ዓይነት ስለነበር በኋላ ላይቀርላቸው ከጀርመን ጋር አንድ ሆነው ይነሱብናል የሚል ፍራቻ ስለነበራቸው ነበር። በሚገርም ሁናቴ ደግሞ የናዚ ጀርመኒ የመስፋፋት ምኞቷን በሚመለከት ኦስትሪያን ለመውረር ብትፈልግ ለጣሊያን ቅርብ ስለሆነች ጣልያን ትቃወመኛለች የሚል ፍርሃት ስለነበረባት የተዳከመች ጣልያን በመፈለጓ በጦርነቱ አዝማሚያ ጊዜ ለኢትዮጵያ እርዳታ ያደረገችው ጀርመኒ ብቻ የሆነችውም በዚሁ ምክንያት ነበር። እውነትም ናዚ ጀርመኒ የጥቁር መንግሥት ለመርዳት ፈልጋ ሳይሆን የጣልያን መንግስት ፈጣን ድልን በኢትዮጵያ ላይ እንዳይቀዳጅና ያ ጦርነት ጣልያንን ያዳክምልኛል የሚል ሂሳብ ስለነበራት ነበር ማለት ነው።

እንግዲህ የሞሶሎኒ ጣልያን በሰላም የሚያደርገው እንቅስቃሴ አለመሳካቱና በኃይል በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያን ማንበርከኩ ለአካባቢው ኃያላን ምንግሥታት ጣልያንን ያስከብርልኛል ለሕዝቤም ሞራሉን ከፍ ያደርጋል ብሎ በማሰብ ከ 1932 ጀምሮ ለጦርነቱ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረግ ጀመረ። ለዚህም ደ ቦኖ የሚባል ፋሺሽት የጣልያን የቅኝ ግዛቶች ሚኒስቴር የነበረውን ወደ ኤርትራ ላከ። ለዚህም ዝግጅት አስከትሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ስርጎ በመግባት ታዋቂ ግለሰቦችን በገንዘብ ማባበል፣ በዘር የመከፋፈል መሠሪ ሥራዎችን ጀመረ። ለምሳሌ ዋናው ጦርነት በተጀመረበት ጊዜ የከዳው የአጼ ኃይለ ሥላሴ አማች የነበረው ደጃች ኃይለ ሥላሤ ጉግሳ የምሥራቅ ትግራይ አስተዳዳሪ፤ የሰሜኑ ገዢ ደጃች አያሌው ብሩ በድብቅ ከጣልያን ጋር መነጋገራቸው ተዋጊውን የኢትዮጵያ ካዳከሙት አንዳንድ ሁናቴዎችና ከማይጨው የመጨረሻው የኢትዮጵያ ሃይል ሲመታ ከኋላ የመቱት በራያና አዘቦ በኩል የኢትዮጵያን ጀግኖች ከኋላ የወጉትን ጣልያን በድብቅ ያስታጠቀቻቸው ባንዳዎች ከላይ እንደገለጽኩት የጣልያን የውስጥ ለውስጥ የሥራ ውጤት ነበር።

ከዚያም የወል ወል ግጭት በጣልያን አነሳሽነት የተፈጠረውም ለወረራው ምክንያት መፍጠሪያ የመጨረሻው የጣልያን ሙከራ ነበር። የወል ወል ግጭት የሆነው የእንግሊዝና የኢትዮጵያ መንግሥቶች በኦጋዴን በጊዜው የኢትዮጵያንና የእንግሊዝ ሶማሊያን ድንበር ለማካለል በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ 100 ኪ/ሜ ገባ ብለው ሊገናኙ ተስማምተው በቦታዊ ሲሄዱ የጣልያን ጦር ከቦታው ቀድሞ በመገኘት፤ ከጣልያን ሶማሌ በኩል ማለት ነው ፍጥጫ ሲፈጥሩና እንግሊዞቹ በመጀመሪያ ተቃውሞ ቢያሰሙም ለኢትዮጵያኑ ጥለው ሲሄዱ ኢትዮጵያኑ እዚያው ፍጥጫውን ቀጥለው በጣልያኖቹ አማካይነት በተተኮሰ ጥይት ምክንያት የተፈጠረ ግጭት ነበር። በዚያም ምክንያት ጣልያን ለዓለም

መንግሥታት ክስ ያቀረበችበትና ዋናው ወረራ እስኪጀበር ድረስ በሊግ ኦፍ ሴሽን ውስጥ ጉዳዩ ሲንጓተት የቆየበትና ጦርነቱም መነሳቱ ስላልቀረ አቋም እንውሰድ በሚል ሰበብ እንግሊዝና ፈረንሳይ፤ በኋላም አሜሪካ በሁለቱም ሀገሮች ላይ የጦር መሣሪያ ዕቀባ ያደረጉበት ሁናቴ ነበር። ይህም ፍርደ ገምድልነታቸው በግልጽ ኢትዮጵያ በጊዜው የራሷን የጦር መሳርያ የማትፈበርክ ስለነበረች የኢትዮጵያ ሕዝብ በባዶ እጁ አይሮፕላኖችን በረድፍ አሰልፋ በብዙ ቶን ቦምብና በጊዜው በዓለም የተከለከለ የመርዝ ጢስ በአርበኞች ላይ ለማርከፍከፍ የሚትችል ሜካናይዝድ ጦር ከነበረው ጦር ጋር ለመጋጠም የተገደዱበት ነበር። እንግዲህ አንባቢያን እንዲረዱልኝ የምፈልገው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፋሺሽስትን ወረራ ሀገሩን ለመከላከል ወደ ጦርነቱ ተገዶ ሲገባ እራሱን የሚከላከልበት መሣሪያ እንኳ እንዳይገዛ በረፈንጆቹ አሻጥር ተደርጎነት ሲሆን፤ በጊዜው በትጥቅ የጣልያን ጦር በሚሊዮን እጅ ቢበልጥም ከብረት የጠነከረ ኢትዮጵያዊ ልቡን ይዞ ነበር የተሰለፈው እንጂ ጣልያን በኃይል ይበልጠናልና እንግዲህ ምን እናድርግ ብሎ እጁን አጣጥፎ የተቀመጠ ሕዝብ አልነበረም።

በጥቅምት ወር 1935 ዓ.ም. የጣልያን መንግሥት የጦርነት ዝግጅቱን በኤርትራ በኩል አጠናቆ ስለጨረሰ ከ 40 ዓመት በፊት መስዋዕት ለሆኑ ጀግኖቻችን ደም መመለሻ በሚል አድዋን በአይሮፕላን በመደብደብ ሞሶሎኒ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ማወጁን በንግግር ለዓለም አስታወቀ። ከዚያም አስከትሎ በፍጥነት ብዙም የተጠናከረ ተከላካይ ጦር በሌላት ኢትዮጵያ ላይ በአይሮፕላን በታንክ እየተረዳ የእግር ጦሩን ወደ ትግራይ በማስገባት ብዙ ስፍራዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ቢቆጣጠርም ለምሳሌ በሰሜን በኩል የተወረወረው በራስ ዕምሩ የሚሚራው ተከላካይ ጦር ወደፊት ይገሠግሥ የነበረውን የጣልያን ጦር በገናው ዘመቻ በመምታት በአንድ ወቅት ኤርትራ ድንበር ቢመልሱትም እንደገና ተጠናክሮ በተለይም በረድፍ ያጠቁ በነበሩ አይሮፕላኖች አማካይነት በብዙ መቶ ቶን የሚቆጠር ቦንብ እንደዝናብ ከሰማይ በማውረድና አስከትሎም በዓለም ተክልክሎ የነበረውን የመርዝ ጢስ በማርከፍከፍ ይጭካኔ ጦርነቱን በመቀጠሉ የራስ ዕምሩ ጦር ተከዜን ተሻግሮ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ተገደደ። ከዚያም በመቀሌ ሠፍሮ የነበረው የራስ ሙሉጌታን ጦር በአሰቃቂ ሁናቴ በመርዝ ጢስ የተረዳው የፋሺሽት ጦር በመምታት በተንቤን በኩል ተሰልፎ የነበረው ን የራስ ካሳና ራስ ስዩም መንገሻን ጦር አሁንም በከፍተኛ ደረጃ የመርዝ ጢሱን እያርከፈከፈ ከሰማይ ቦምብ ያዘንብ በነበሩት 200 ያህል አይሮፕላኖች አማካይነት በተንቤን የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር ተመታ። ይህ ሁሉ ሲሆን ኢትዮጵያውያን የጦርነቱ መክፋት፤ የጣልያን ጦር በቴክኖሎጂ ከፍተኛውን ቦታ መያዝና ሰማዩን መቆጣጠርና የመርዝ ጢስ በላያቸው ላይ መዝነብ ተስፋ አስቆርጧቸው የቆሙበትና በር ከፍተው የሰጡበት ወቅት አልነበረም። እንዲያውም ብዙዎቹ ጀግንነትን እየሠሩ ያለፉበት ወቅት ነው። እኔን የሚገርመኝ ዛሬ ከነኦነግ ጋር ለመሰለፍ ያሰፈሰፉት ዶ/ሮች ያንን ታሪክ ሲያጣጥሉ እንዲያው በዚያን ወቅት ኖረው ቢሆን ኖሮ ለኢትዮጵያውያን ምን ምክር ይሰጡ ይሆን ነበር? ማፈሪያ ሁላ! ዛሬ ለጎሰኝነት ፓለቲካ እጃችንን እንስጥ ያሉ ለጣልያኖች እጃችንን እንስጥ ማለታቸው አይቀርም ነበር።

እንግዲህ ወደ መሃል ሀገር በዚህ ዓይነት እየገሠገሠ የነበረውን ጦር ለመከላከል የመጨረሻው የኢትዮጵያ የሰሜን ጦር በማይጨው የነበረው ነበር። የማይጨው ጦርነት እንግዲህ የመጨረሻው የኢትዮጵያ ደጀን ጦር የአጼ ኃይለሥላሴው የክብር ዘበኛውን ጨምሮ መሽጎ የተቀመጠውን የጣልያን ጦር ላይ ምሽጉን ጥሶ በመግባት ለመጨረሻ ጊዜ ጣልያንን ለመቋቋም የተደረገ ያባቶቻችን የሞት የሽረት ጥረት ነበር። ብርሃኑ ነጋ ጣልያን ያቸነፈን ቦታ አድርጎ በማቅረብ የምናፍርበት ነው ብሎ ሊያስተምር የሞከረው ታሪክ አባቶቻችን ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉበት ቦታ ነው። የኢትዮጵያ ጦር ምሽጉን ጥሶ ለመግባት ያደረገው ጥረት አልሳካ ብሎ (ከሰማይ ይወርድባቸው የነበረው ቦንብና የመርዝ ጢስ፣ ጠላት የደረደረው የካባድ መሳሪያ ብዛት። እንዲሁም ከጠላት ጋር አብረው የነበሩት ባንዶች ለጣልያን የኢትዮጵያን ምስጢር ይሰጡ ነበርና) ወደ ኋላ ሲያፈገፍጉ ደግሞ በራያና አዘቦ በኩል ጣልያን ባስታጠቃቸው ባንዶች የሚያፈገፍገው የኢትዮጵያ ጀግኖች ጦር በራሱ ወገን የተመታበት ከሁሉም በላይ ማይጨውን በታሪካችን የምናከብርበት ምክንያት የጣልያን አይሮፕላኖች የሚያፈገፍገውን ጦርና አካባቢውን ለቆ የሚሄደው ወገናችንን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ እየተዝዙ

ባለበት ወቅት በአሸንጌ ሜዳ ላይ በቦምብ ባከታታይ የደበደቡበት፣ ከዚያም የተረፈውን በመርዝ ጢስ የጨረሱበት አሳዛኝ የመስዋዕትነት ምት ነበር። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ይህንን የመስዋዕትነት ማይጨውን የሚያስታውሰው በዚህ ሁናቴ እንጂ ታሪክ አላዋቂዎች በሚተርኩልን የመሸነፍ የሀፍረት ታሪካችን ከቶውንም ሊሆን አይችልም። ጀግኖች አባቶቻችን በዚህ ታሪካዊ ቦታ ከፍተኛ ምስዋዕትነት ያስከፈላቸው ትንንቅ ጠላትን ወደ መሃል ሀገር ከመዝለቅ ባይገታውምና አፄ ኃይለሥላሤም ንጉሣዊ ቤተሰቦቻቸውንና የቅርብ መኳንንቶቻቸውን አስከትለው ባስቸኳይ አዲስ አበባ ከዚያም ወደ ጅቡቲ፤ ከጅቡቲም የእንግሊዝ መንግሥት በሞግዚትነት ያስተዳድራት በነበረች መርከብ ወደ እንግሊዝ ሀገር ቢሄዱም፤ መሪ አጣን፣ ጠላት ጠነከረብን ወይም ተሸንፈናል ብለው እጃቸውን አልሰጡም ነበር። እንዲያውም ከዘያ በኋላ ለሚቀጥለው አምስት አመት ከፍተኛ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ትንንቅ አድርገው ለነጻነት አብቅተውናል።

በነገራችን ላይ ጣልያንን በሰማይ ሲያዘንብ ከነበረው ቦምብ በላይ የበላይነቱን የሰጠው በተጨማሪ ያዥጎደጎደው የመርዝ ጢስ ነበር። የመርዝ ጢስን በመጠቀም በኩል የጣልያን መንግሥት በጊዜውም ቢከደውም የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ያጋለጠው ጉዳይ ነበር። የፋሺሽቱ መንግሥት ይህንን በሚመለከት በሃገሩ ጋዜጦች እንዳይዘገቡ አድርጎ ክድቶ ቆይቶ ነበር። ከ 60 ዓመት በኋላ በ 1995 ዓ.ም. ፕሮፌሰር ዴል ቦካ በሚባል አንድ ጣልያናዊ የማያቋርጥ ክትትልና ጥረት የጣልያን የመከላከያ ሚኒስቴር ጣልያን በፋሺሽቱ ወረራ ወቅት የመርዝ ጢስ በኢትዮጵያውያን ላይ እንደ ተጠቀመች አምኗል። በጦርነቱ ወቅትም የምዕራባውያን የቀይ መስቀል ድንኳኖች ሳይቀሩ የተመቱበት ስለነበር የዓለም መንግሥታት ጠንቅቀው ያውቁት ነበር። ነገር ግን የሊግ ኦፍ ኔሽን እንኳን ጣልያን ስለተጠቀመችበት አግባብ ያልሆነ የመርዝ ጢስ መሳሪያ ቀርቶ የጦርነቱም አነሳስ ሊያስወግዛትና ጠንካራ ዕቀባ ሊያስደርግባት ሲገባ ዕቀባ አይሉት ነገር ውሳኔ አሳልፈው ነበር። ዕቀባው የጣልያንን መንግሥት ጦርነቱን ሊያስቆመው በሚችል ሁናቴ የተወሰነም አልነበረም። ለምሳሌ የሱዊዝ ቦይን በመዝጋትና የነዳጅ ዘይት ዕቀባ እንዲደረግ አልተወሰነም ነበር። ይህም እነ ዶ/ሩ ዛሬ "***በትርጉማቸው***" ሌላ ሊያስተምሩን ካልፈለጉ በስተቀር ፈረንጆቹ በኢትዮጵያውያን ላይ ክህደትንና በግልጽ የቆሙት ከጣልያን ፋሺሽት ጋር ነበር ማለት ይቻላል። ዶ/ሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠራጣሪ ነው ብሎ በዚሁ ንግግሩ እንደመጥፎ ባሕሪያችን ቆጥሮ ሊያለሳልሰን ጥረት አድርጎአል። ምናልባትም ዛሬ ኦነግንና ኦብነግን እመኗቸው ለማለት አስቦ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን መታወቅ ያለበት ሃቅ ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነት ላይ ፈረንጆችንም፣ የፈረንጅ አሽከር ለመሆን የሚሯሯጡትንም ሆነ፣ የጎሣ ፖለቲከኞችንና አጫፋሪዎቻቸውን ***<u>አያምንም</u>***።

**ለማጠቃለል፦**

ከላይ እንደገለጽኩት የዚህ ጽሁፍ ዋና ዓላማ ዶ/ር ብርሃኑ ዛሬ አብሮ እሠራለሁ የሚላቸውን ኦነግንና ኦብነግን ለማስደሰት ወይም ታማኝነቱን ለማረጋገጥ ሲል የኢትዮጵያን ታሪክ የማንቋሸሽ ምንም መብት እንደሌለው ያለውን ዕውነታ በማቅረብ በዶ/ር ነቱ ዓምነውት የሚከተሉትን ወጣቶች ግንዛቤን እንዲያገኙበት ለማድረግ ነው። አንባቢያንን የማሳስበው ከዚህ በላይ ያቀረብኩት የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በዓለም ተዘግቦ የተቀመጠ ስለሆነ በነጻው ዓለም ተቀምጠን ማንበብ የምንችል ሁላ ኢትዮጵያውያን ያስተማሩን ታሪክ የውሸት እንኳ ተደርጎ ቢቀርብ ልናረጋግጥ የምንችልበት ክፍለ ዓለም ነው ያለነውና ዶ/ሩ ብለዋልና ዕውነት መሆን አለበት በሚል ፈሊጥ ራሳችንን እንዳናጃጅል ለማስገንዘብም ጭምር ነው። እኔ ራሴን እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ ጠቢብ አድርጌ የምቆጥር አይደለሁም። ብዙ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በዓለም ዚሪያ እንዳሉ አውቃለሁ። ከሁሉም በላይ የጽሁፌ ዓላማ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያዊነት ዘብ ይቁም የሚል ጥሪ ለማስተጋባትም ጭምር ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ በመሸራረፍ ነፃ አውጪ ነን የሚሉን ስብስቦች ባላፈው 20 ዓመታት በሀገራችን ላይ እያደረሱት ያሉትን ጥፋት በዝምታና በይሉኝታ ቁጭ ብለን መመልከቱ ያብቃ!

አቶሰውየው ባላገሩ (ከሰሜን አሜሪካ ነኀሴ ፳፯- September 2, 2011)

እምቢኝ ለወያኔዎች!

እምቢኝ ለጎሠኝነት ፖለቲከኞችና አጫፋሪዎቻቸው!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በዕውነተኛ ልጆቿ ትግልና ምስዋዕትነት እንደገና ያብባል!